UNITED NATIONS
HUMAN RIGHTS COUNCIL

# የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ፕሬዝዳንት መሀመድ ቻንዴ ኦትማንን የኢትዮጵያ ኮሚሽን ሊቀመንበር አድርገው ሾሙ

**12 ታህሳስ 2015**

**ጄኔቫ (ታህሳስ 12 ቀን 2015**) የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ፕሬዝዳንት አምባሳደር ፌዴሪኮ ቪሌጋስ (አርጀንቲና) ታንዛኒያውን ሚስተር ሞሃመድ ቻንዴ ኦትማን በኢትዮጵያ ጉዳይ ምክር ቤት የፈጠረው የሰብአዊ **መብት ኤክስፐርቶች ኮሚሽን** ሊቀመንበር አድርገው እንዲሾሙ ወሰኑ።

የአቶ ኦትማን ሹመት የመጣው ካሪ ቤቲ ሙሩንጊ የኮሚሽኑ ሊቀመንበር እና አባል ሆነው መልቀቃቸውን ተከትሎ ነው። አምባሳደር ቪሌጋስ ወ/ሮ ሙሩንጊ በኮሚሽኑ ላበረከቱት ሚና አመሰግናለው ወደፊት በሚያደርጉት ጥረት መልካም ይመኛል።

የታንዛኒያ የቀድሞ ዋና ዳኛ እ.ኤ.አ (2010-2017) ሚስተር ኦትማን በተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሃፊ ባን-ኪ ሙን. እ.ኤ.አ. በ 2019-2020 የዓለም አቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት እና የሮማ ስምምነት ስርዓት ገለልተኛ ኤክስፐርት ግምገማ አባል ሆኖ አገልግሏል ፣ በአለም አቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት የሮም ስምምነት የመንግስት ፓርቲዎች ምክር ቤት የተሾመ ።

የአቶ ኦትማን የቀድሞ ልምድ የቲሞር-ሌስቴ እ.ኤ.አ (2000-2001) አቃቤ ህግ፣ የሩዋንዳ አለምአቀፍ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት ክስ ሃላፊ እ.ኤ.አ (1998-2000) እና የዩኤንዲፒ-ካምቦዲያ ከፍተኛ የህግ እና የፍትህ ዘርፍ አማካሪን ያካትታል። እ.ኤ.አ. በ 2006 የእስራኤል እና ሊባኖስ የትጥቅ ግጭትን ተከትሎ በሊባኖስ ያለውን ሁኔታ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ከፍተኛ ደረጃ አጣሪ ኮሚሽን አባል እና የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት በሱዳን የሰብአዊ መብት ሁኔታ ገለልተኛ ኤክስፐርት በመሆን አገልግለዋል ። እ.ኤ.አ (2009-2010)

በኢትዮጵያ ላይ የሶስት ሰዎች የሰብአዊ መብት ኤክስፐርቶች ኮሚሽን በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ታኅሣሥ 08 ቀን 2014 በኢትዮጵያ በግጭቱ ውስጥ በተሳተፉ አካላት ጥቅምት 24 ቀን 2013 ጀምሮ ተፈጽሟል ያለውን የሰብአዊ መብት ጥሰት እና የመብት ጥሰት የማጣራት ሥልጣን ተሰጠቶት **ተመስርተዋል**። እ.ኤ.አ. መስከረም 27 ቀን 2015 ምክር ቤቱ የኮሚሽኑን ስልጣን ለተጨማሪ ለአንድ አመት **ለማደስ** ወስኗል።

ኮሚሽኑ በ52ኛ መደበኛ ጉባኤው (የካቲት 19 እስከ መጋቢት 22 ቀን 2016) ቀጣዩን ወቅታዊ መረጃ ለሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ለማቅረብ ቀጠሮ ተይዞለታል።

******

ለተጨማሪ መረጃ ጥያቄ እና ሚድያን፡ እባክዎትን ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ሰዎች ይጠይቁ፡ ሮናልዶ ጎሜዝ የICHREE
rolando.gomez@un.org፡ +41 (0) 22 917 9711 ቶድ ፒትማን፡ የሚድያ አማካሪ፡
todd.pitman@un.org ማቲው ብራውን ፡ የHRC ህዝባዊ መረጃ ሃላፊ
matthew.brown@un.org፡ ወይም ፓስካል ሲም፡ የICHREE ሕዝባዊ መረጃ ሚድያ ሃላፊ፡simp@un.org